*ፓኖራማ ቁጥር 48*

*የትዝብት አድማስ*

*ጥቅምት 21 ቀን 2001 ዓም*

## *<u>አማራጭን መምረጥ</u>*

## *<u>ጋሪው ፈረሱን ባይቀድም</u>*

*የየትኛውም ሀገር ሕዝብ በታሪኩ ልክ እንደ አሁኑ እንደኛው ብሔራዊ ችግርና ጥፋት ሲያጋጥመው፥ ሀገሩን ከጥፋት ለማዳን በሚደረገው ትግል፥ የተለያዩ አማራጮችን መፈለግ የነበረና ያለ ነው፡፡ እኛም ዛሬ በዚህ ክስተት ውስጥ መግባታችን የሚጠበቅ በመሆኑ ሊያስገርም አይችልም፡፡ ለችግራችን መፍትሄ ፍለጋ በምናደርገው ውጣ ውረድ፥ የተለያዩ አቅጣጫዎችን በመመልከት፥ በርካታ አማራጮችን እያየንና እየመዘን ከጊዜውና ከአቅም አኳያም እየገመገምን የሚያዋጣውንና ትክክለኛውን አማራጭ መምረጥ አስፈላጊና ተገቢ መሆኑን እናምንበታለን፡፡ በመሆኑም፥ይህንን ለሀገር ወዳድ ወገኖቻችን ማስረዳትና አስተያየታችንንም መጠቆም ግዴታችን እንደሚሆንም እንረዳለን፡፡ ከዚህ አኳያ ስንነሳ፥ በየጊዜው በሀገር ወዳድ ወገኖቻችን መካከል በሚደረገው ብሄራዊ ውይይት ውስጥ እንደ ዜግነታችን የበኩላችንን አስተያየት መስጠትና ውጤት ሊያስገኝልን የሚችለውን አማራጭ መምረጥ የትግላችን ግዳጅ ነው ብለን ወስነናል፡፡*

*ሀገራችንን ከዘረኞች ከፋፋይና በታኝ ሴራ ለማዳን፥ ወሳኝ ርምጃ ለመውሰድ የሚያስችለንን አማራጭ መምረጥ ወቅታዊና አጣዳፊ መሆኑ አንድና ሁለት የሚባል አይደለም፡፡አንዳንዶች አቋማችንንና ምርጫችንን ስንገልጥ*

“በማየገባችሁ ገባችሁ፤ጣልቃ ገባችሁ” በሚል የሚዘነዘሩብንንም ክስ የምንቀበለው አይደለም፡፡ የሀገራችን ጉዳይ ይመለከተናል፤ያገባናልናም ነው፡፡ በመሆኑም፥ ከአማራጮቹ ሁሉ በቅድሚያ ሊመረጥ የሚገባው አማራጭ፥ ወያኔን  በሁለገብ ትግል እያጣዳፉ ማስወገድና ኢትዮጵያን ከጥፋት ማዳን ነው፡፡ከአማራጮቹ ሁሉ ቅድሚያ የሚሰጠው ይህ አማራጭ መሆኑንም የኢትዮጵያ ሕዝብ መርጦ ጨርሷል፡፡ በአሁኑ ወቅት ከዚህ የተሻለ አማራጭ ሊኖር ይገባል ተብሎ ጊዜንና ጉልበትን ማበከን፥ ለወያኔ እፎይታ እንደመስጠት ነው ብለው የሚናገሩ የፖለቲካ ጠበብት ቁጥራቸው  እየበረከተ በመሄድም ላይ ይገኛል፡፡ አንድ አንድ ወገኖች ኢትዮጵያን ከአለችበት ማጥ ለማዳንም ይሁን ወይም በተለያዩ ምክንያቶች፥ የቅድሚያ ምርጫቸው ፥በሆነ ብሄረሰብ ላይ ተባብሮ መነሳት ወይም ድርጅት አልባ ንቅናቄ መመስረት ወይም የስደት መንግሥት ማቋቋም  ነው ሲሉ ይደመጣል፡፡ከዚህም የተነሳ ሁኔታውን በቅጡ ካለመረዳትም ይሁን ከቁጭት በመነሳት ኃሳቦች እየተንሸራሸሩ ናቸው፡፡  የቀቢፀ ተስፋና የወያኔ ዘረኝነት ሌላ ገፅ የሆነውን የፍጅት አማራጭ ወደጎን ስንተው፥ በሌላ በኩል ድርጅቶች አልባ ትግልም ውጤታማ እንደማይሆን የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በመሠረቱ የስደት መንግሥት ምርጫ በራሱ  እንዲያው በደፈናው መጥፎ ምርጫ ነው ተብሎ ሊባል እንደማይችል በታሪክ አጋጣሚዎች የተመሠረቱትን የስደት መንግሥታትንና ሚናቸውንም መጥቀስ ይቻላል፡፡   ነገር ግን የስደት መንግሥት ማቋቋም ለትግላችን ውጤት ያስመዘግባል ተብሎ ከታመነበትና ያንንም አማራጭ መውሰድ አስገዳጅ ነው የሚል ውሳኔ ከመደረሱ በፊት፥ወቅታዊውንና ተጨባች ሁኔታዎችን መገምገም ወሳኝ ነው፡፡ከሁሉ አስቀድሞ፥የሀገር ውስጥ የአካባቢንና የዓለም አቀፍ ነባራዊና ተጨባጭ ሁኔታዎችን በቅጡ መገንዘብ ወሳኝ ይሆናል፡፡ ለነገሩ የተመሰሩቱት ወይም ጊዜው ሲጠይቅ መመስረት ያለበት ጊዜያዊ ወይም የጋራ ህብረት ጊዜያዊ መንግሥት መባሉ የተመረጠ ይሆናል፡፡  ከዚህ ግንዛቤ በኋላ፥ በደፈናው ጊዜያዊ መንግሥት የሚባለውንም ለማቋቋም፥ቢያንስ የሚከተሉት መሠራዊ ጉዳዮች ተሟልተው እንዲገኙ ያስፈልጋል፡፡

1. ጊዜያዊ መንግሥት መቋቋም አለበት የሚለው ክፍል( አመራር) (ክፍሎች) እርሱ እራሱ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅትና ተዋጊ ሠራዊት ወይም እየመራው ያለ ጠንካራ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እንዲኖረው ማስፈለጉ ብቻ ሳይሆን ይህ አመራር ቢያንስ የተወሰኑ መንግሥታትን እውቅና እንዲኖረው ያስፈልጋል።

2. ይህ ኃይል ነፃ ያወጣው ሕዝብና የተወሰነም ቢሆን፥የሚቆጣጠረው የሀገሪቱ ነፃ መሬትና የግዛት ክልል ሊኖረው ይገባል። ነፃ ያወጣው ሕዝብም ሁለንተናዊ ድጋፍ መስጠቱ ወሳኝነት አለው። ሁለንተናዊ ድጋፍ ሲባል፤ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ብቻ ሳይሆን፥ጠላትን ለመፋለም በሚደረገው ሕዝባዊና የትጥቅ ትግል ያለተቋረጠና የህይወት መሥዋዕት የሚጠይቀውንም ሁሉ ተሳትፎ እንዲያደርግ ይጠበቅበታል ማለት ነው።

3. ይህ የሚቋቋመው ጊዜያዊ መንግሥት፥ያልተቋረጠ የፖለቲካ፥ የዲፕሎማቲክ፥ የገንዘብ፥ የጦር መሳሪያና ሌሎቹም አስፈላጊ የሆኑ የቁሳቁስ ርዳታና ትብብር ማግኘት አለበት። ዛሬ ኢትዮጵያ ሀገራችን፥ ከላይ የተጠቀሱትን ድጋፎችና ትብብሮች ሊያደረግላት የሚችል የቅርብ ጎረቤትም ይሁን የዕሩቅ ዘመድ እንደሌላት የኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ በሚገባ እያወቀው፥ ይህ ሁሉ ትብብርና ርዳታ ይገኛል ብለን እኛ በበኩላችን፥ ቢያንስ ራሳችንን የመንደለል ዜጎች ልንሆን አይገባንም። ከዚህም አልፎ ተርፎ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከበታኝ ዘረኞች ሴራ ለማዳን የሚቆረቆርልን ክፍልም ይሁን መንግሥት አለ ብለን አናምንም። እንዲያውም፥ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፥ ዜጎቿም እንደ ሕዝብ እንዳይኖሩ ተግተው የሚሰሩ ጠላቶች እንዳሉ፥ ቢያንስ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን/ያት የሚሰወር ሊሆን አይችልም። ይህንም ሁሉ ተገንዘበን፥ ብሎም ይህ ዛሬ የሚደረገው ትግል፥ የብሄራዊ የነፃነትና የዴሞክራሲም ትግል መሆኑን በሚገባ ተገንዝበን፥ለዚሁ ትግል የሚያስፈለገውንና ድልም ልንጎናፀፍበት የሚያስችለንን ዓይነተኛውን አማራጭ

*መውሰድ አስፈላጊያችን ነው፡፡*

*ለብሔራዊ የነፃነትና የዴሞክራሲ ትግል ራሳቸውን ያዘጋጁ ሕዝቦች፥ በሚያደርጉት ጥረት እንደ አስፈላጊነቱና እንደ ሁኔታው ጊዜያዊ ወይም የሽግግር መንግሥታት እየቋቋሙ ዓላማቸውን ከግብ በማድረስ መታገል ይችላሉ፡፡ ለዚህም እንደ ዓይነተኛ ምሳሌ የሚጠቀሰው፥የአልጀርያ ነፃ አውጭ አርበኞች፥የአልጀርያን ሕዝብ ከፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ነፃ ለመውጣት ያስቻላቸውን ጊዜያዊ መንግሥት/ጉቨርንማ ፕሮቪሸዋር/መመስረታቸው ነው፡፡*

*የአልጀርያን የነፃነት ትግል በመምራት ድልን እንዲጎናፀፍ ያስቻለው፥ __የአልጀርያ ብሄራዊ የነፃነት ግንባር__ **ተብሎ የሚጠራው ጠንካራ ድርጅት ነበር፡፡** በትግላቸው ሂደትም፥ ከላይ የተጠቀሱትን ለጊዜያዊ መንግሥት መሠረት የነበሩትን መስፈርቶች አሟልተው በመገኘታቸው ጊዜያዊ መንግሥት መስርተው፥ ሀገራቸውን አልጀርያን ከአያሌ ዘመናት የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት አላቅቀው፥ ሕዝባቸውን ከባርነት ቀንበር አውጥተው ብሄራዊ ነፃነታቸውን ተጎናጽፈዋል፡፡ የቪየትናም ታጋዮችም ጊዜያዊ መንግሥት ያቋቋሙት፥ በትጥቅ ትግል ሀገራቸውን ነፃ እያወጡ በመሄድ ላይ ሳሉና በቻይናና ሶቭየት ህብረትም ወዘተ ተደግፈው ነበር፡፡ ኢሕአፓም ቢሆን ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥትን አማራጭ ያቀረበው ሕዝባዊ ትግሉ አይሎ በነበረበትና የሽግግር መንግሥትም ይቋቋም ያለው፥ የነበረው አገዛዝ ሊንኮታኮት ሲልና በነፃ መሬቱም ላይ ሆኖ መሆኑ መረሳት የለበትም፡፡*

*ታሪክ ይጠቀስ ከተባለ፥ የስደት መንግሥት በሚል የተቋቋሙ በአብዮት ሽንፈት ደርሶባቸው ወደ ምዕራብ አውሮጳ የተሰደዱ መሳፍንትና የንጉሣን ቤተሰቦች ነበሩ፡፡ ያው መና ቀርተዋልም፡፡ይህንን ሁሉ መጥቀሳችን ፥ከራሳችን ወቅታዊው ሁኔታ ጋር የንፅፅር ትንታኔ እንድናይበት የሚያስችለንን ግንዛቤ ለማግኘት እንድንችል ለማለት ነው፡፡ ከዚህም በላይ፥ ጊዜያዊ መንግሥት ለማቋቋም ምን ምን መስፈርቶች ማሟላት እንዳለባቸው ለማስመዝገብና ይህ*

*ጉዳይ ደግሞ በተለይ በእኛ ሀገር ለአሁኑ ነባራዊ ሁኔታ ምላሽ ነው ተብሎ ከተገፋ፥ ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያጋድል መሆኑንም ለመጠቆም ነው።*

*በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ሲታይ፥የቅድሚያ ምርጫችን በጊዜያዊ ወይም በሽግግር መንግሥት ማቋቋም ላይ ማተኩሩ፥ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያጋድላል ሲባል፥ በዋናው ምርጫችንና አጀንዳችን ላይ እንዳናተኩር ኃይላችንንና  ጥረታችንን ይከፋፍልብናል ለማለት ነው።ይህ ደግሞ በብሄራዊ ነፃነት ትግላችን ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ አንደምታ በቀላል የሚገመት አይሆንም።*

*የጊዜያዊ መንግሥትን ለመመሥረት የሚያስፈልጉትን መሠረታዊ ጉዳዮች ከሞላ ጎደል ለመገንዘብ ከቻልን ዘንድ፥ ይህ ጉዳይ በአሁኑ ወቀት ሀገራችንን ከጥፋት ለማዳን በሚደረገው ሀገራዊ ትግል የመጀመሪያ ምርጫችን ለምን ሊሆን እንደማይገባው አንድ አንድ ነጥቦችን ማየት የሚገባ ይሆናል። ለዚህም የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ መዳሰስ ወሳኝ ሊሆን ነው።*

1. *ጊዜያዊ መንግሥት መቋቋም አለበት ብሎ  የሚያስበው ኃይል፥ እርሱ እራሱ ጠንካራ ፖለቲካዊም ሆነ ወታደራዊ ኃይል መሆኑን በተግባር አስመስክሮ አላሳየም። ስለሆነም የውጭም ይሁን የሀገር ውስጥ ርዳታና ትብብር ቀርቶ ዕውቅናም የማግኘት ዕድል የሚኖረው ይደለም።*

2. *መንግሥት ተብሎ የሚጠራው ተቋም፥መንግሥት ከሚያሰኙት መስፈርቶች መካከል፥ ሀ) የሚመራው ጠንካራ ሕዝባዊ አንቅስቃሴ መኖሩ፤*

   *ለ)  የሚቆጣጠረው ነፃ መሬት ( ግዛት)  አስፈላጊነቱ እና*

   *ሐ)  የሚያስተዳድረው ሕዝብ መኖራቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው።*

*በአሁኑ ወቅት፥ ይህንን አሟልቻለሁ ብሎ አፉን ሞልቶ የሚናገርና ሊታመን የሚችል ማንም ድርጅት እንደሌለ ለሁሉም ዜጋ ግልፅ ነው።*

*ታዲያ እነኝህ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ ጊዜያዊ ወይም የስደት መንግሥት ማቋቋም ጉዳይ ለኢትዮጵያ ትግል የመጀመሪያው ምርጫ ሊሆን ይገባል ተብሎ የሚገመት አይሆንም፡፡ በዚህ ድምዳሜ ሁሉም የጋራ ስምምነት መድረስ ከቻለ፥በሚደረገው ሀገር አድን ትግል ከሁሉ በፊት ሊኖረን የሚገባን ምርጫ ምን ሊሆን ይችላል? ብለን በመጠየቅ የመጀመሪያው የትግላችን አጀንዳንና ምርጫንን ማወቅና በቅደም ተከተል እያስገባን መታገል የወቅቱ የሕዝብ ጥያቄ መሆኑን ማመን አለብን፡፡ በመሆኑም፥ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች በማያሻማ ሁኔታ በግልፅ መቀመጥ አለባቸው፡፡*

1. *ወያኔን በሁለገብ ትግል እያጠቁ ማስወገድና ኢትዮጵያን ከጥፋት ማዳን የቅድሚያ አጀንዳችን ነው የሚሉና በኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነትና አንድነት የሚያምኑ ድርጅቶች ትግሉን ማፋፋም አለባቸው፡፡*

2. *እነኝህ ድርጅቶች ደግሞ በጥገናዊ ለውጥ ከሚያምኑና ሁለት ባላዎችን ይዘው ከሚውገረገሩ ድርጅቶች ጋር ያሏቸውን መሠረታዊ ልዩነቶች "እናጣጥማለን፥ እናስታርቃለን፥ እናቻችላለን፥ እንጣመራለን፥ኅብረት እንፈጥራለን" የሚሉትን ዝባዝንኬ ማቆም የመጀመሪያው ውሳኔያቸው ሊያደርጉት የግድ ይላል፡፡*

*በአሁኑ ወቅት የትግሉ ምዕራፍ የደረሰበትን ደረጃ በሚገባ ስናጤን፥እነዚህ ሁለት ጎራዎች ምንነታቸውንና ማንነታቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ለይቶ አውቋቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ድርጅት ትክክለኛ ማንነቱን ለመደበቅ በተለያየ ጭምብል የሚጋረድበት ሁኔታ የለም ዛሬ፡፡ "በጨው ደንደስ በርበሬ የሚወደስበት" የትግል ሂደት ቀርቷል፡፡ አክትሟል፡፡ ዛሬ፥ አንዱ ሌላውን የሚያታልልበት ወቅት አይደለም፡፡ ሁሉም ተዋውቋልና! ስለሆነም ዛሬ፡-* ***ምርጫችን አንድ፥ አጀንዳችን ግልፅ፥ ትግላችን መራራ፥ ራዕያችን ከአድማስ ባሻገርና ሀገር-አቀፍ፥ ኢላማችን ወያኔ፥ የመጨረሻው ግባችን ሀገራችንና***

***ሕዝባችን ከዘረኞች ጥፋት ማዳን ነው፡፡ ለትግላችን ሌላ አልፋና ኦሜጋ ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም፥ ምርጫውንና ጎዳናውን ያልለየ ትግል ግቡን አይመታምና ፥ትክክለኛውን ምርጫ በመምረጥ ብሔራዊ የትግል አጀንዳችንን በቅደም ተከተል እያስገባን፥ መራራውን ትግል ከማካሄድ ሌላ አማራጭ የለንም፡፡ ጋሪው ከፈረሱ ከቀደመ የትም መጓዝ አይቻልምና ትግላችን ግቡን ለመምታት እንዲችል፥ ምርጫችን እንምረጥ!!!***